መልእክት አራት

## በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ያሉ ውስጠ-ልምምዳዊ እውነቶች ምለሳ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዮሐ. 1፡14፣ 16፤ 14፡16-20፣ 6፤ 20፡22፤ 4፡10፣ 14፤ 6፡35፣ 57፤ 12፡23-24፤ 3፡29-30

**I. ጌታ በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ ያሉትን ውስጠ-ልምምዳዊ እውነቶችን መመለስ ይፈልጋል—ዮሐ. 1፡14፤ 14፡16-20፤ 1 ጢሞ. 3፡15-16፤ 2 ጢሞ. 4፡22፤ 3፤15-16፦**

ሀ. በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ ያሉ እውነቶች ሁልጊዜም ባለ ሁለት ገጽታ ናቸው—ውጫዊው ገጽታና ውስጠ-ልምምዳዊው ገጽታ—ሮሜ. 8፡34፣ 10፤ ቆላ. 3፡1፤ 1፡27፦

1. የእግዚአብሔር ማዳን ሁለት ገጽታዎች አሉት፦ በምርጡ ልብስ የተመለከተው የውጪው፣ ውጫዊው ገጽታ፣ እና በሰባው ፍሪዳ የተመለከተው ውስጣዊው፣ ውስጠ-ልምምዳዊው ገጽታ፤ ክርስቶስ እንደ ውጫዊው ጽድቃችን ውጫዊ በሆነ መልኩ ድነታችን ሲሆን፣ ክርስቶስ ለድሰታችን እንደሆነ ውስጠ-ልምምዳዊው ሕይወታችን ውስጣዊው ድነታችን ነው።
2. ውጫዊ አስተምህሮዎች ሁሉ ለውስጠ-ልምምዳዊው ልምምዳችን ናቸው፤ ውጫዊው ክርስቶስ ንስሐ የገባ ኃጢአተኛን ለመሸፈን የሆነ እግዚአብሔርን የሚያረካው ጽድቅ "ምርጡ ልብስ" ሲሆን (ኤር. 23፡6፤ 1 ቆሮ. 1፡30)፣ ውስጠ-ልምምዳዊው ክርስቶስ ደግሞ እንደ ብልጡጉ ክርስቶስ (ኤፌ. 3፡8)፣ በትንሣኤ ለአማኞች የሕይወት አቅርቦትና ድሰታ በመስቀል ላይ የተገደለው "የሰባው ፍሪዳ" ነው (ዮሐ. 10፡10፤ 6፡63፤ 11፡25፤ 12፡24፤ 4፡10፣ 14፤ 20፡22)።
3. ክርስቶስ እንደ ውጫዊው ጽድቃችን የጻድቁን እግዚአብሔር ጥያቄዎች ለማሟላት የሚያስችለን ሲሆን፣ ክርስቶስ እንደ ውስጠ-ልምምዳዊው ጽድቃችን የድል-ነሺውን ክርስቶስ ጥያቄዎች እንድናሟላ ያስችለናል—መዝ. 45፡13-14፤ ፊልጵ. 3፡9፤ ራእ. 19፡7-9።
4. መጽደቅ "ከሕይወት" ነው ምክንያቱም ሕይወት የእግዚአብሔር ማዳን ግብ ነውና፤ ከጌታ ጋር እና በጌታ ውስጥ የሆነው ሕይወታዊው የሕይወት ጥምረታችን ውጫዊ በሆነ መልኩ የመጽደቃችን ውጤት ነው—ሮሜ 5፡10፣ 17-18፤ 11፡17፣ 24፤ ዮሐ. 15፡4-5፤ 1 ቆሮ. 6፡17።

ለ. ውስጠ-ልምምዳዊዎቹ እውነቶች ከመንፈስና ከሕይወት ጋር የተያያዙ እና በመንፈስና በሕይወት የተቀናበሩ ናቸው—ዮሐ. 6፡63፤ 2 ቆሮ. 3፡6፦

1. መንፈስና ሕይወት የውስጠ-ልምምዳዊዎቹ እውነቶች ንጥረ-ነገሮች ናቸው፤ ስለዚህ ያለ መንፈስና ሕይወት ምንም አይነት ውስጠ-ልምምዳዊ እውነቶች የሉንም።
2. በመንፈስ እና በሕይወት ስንኖር፣ የውስጠ-ልምምዳዊዎቹ እውነቶች ልምምድ አለን፣ ይህም የቤተ ክርስቲያን ሕይወትን ያመጣል—ሮሜ 8፡2፣ 4፤ 16፡1፣ 4-5።

**II. የዮሐንስ ወንጌል—በውስጠ-ልምምዳዊ እውነቶች ላይ የሚያተኩረው መጽሐፍ—የክርስቶስ ውስጠ-ልምምዳዊ ልምምዶች ሊኖረን እንደሚገባ ይገልጣል—4፡14፤ 6፡57፤ 20፡22፦**

ሀ. የዮሐንስ ወንጌል ውስጠ-ልምምዳዊ በሆነ መልኩ ክርስቶስን እንደ ሕይወት መለማመድ ላይ ያተኮረ መጽሐፍ ነው—1፡4፤ 3፡15-16፤ 10፡10፤ 11፡25፤ 14፡6፦

1. አብ የሕይወት ምንጭ ነው፣ ወልድ የሕይወት አካል መልበስ ነው፣ መንፈስ ሕይወት ሰጪው ነው—5፡26፤ 1፡4፤ 6፡63።
2. የክርስቶስ አካል መገንባትና መጨመር የሕይወት ማደግና ሞልቶ መፍሰስ ናቸው—7፡37-38፤ 15፡1-8።
3. ድል-ነሺዎቹ ለምለሙ የሕይወት መስክ የሆነው የክርስቶስ ተቀባዮች፣ ተደሳቾች እና አዳዮች ናቸው—1፡12-13፣ 16፤ 10፡9-10፤ 21፡15-17።
4. አብ እንደ ሕይወት ምንጭ ምንጩ ነው፣ ወልድ እንደ ሕይወት መፍለቅ ፍልቁ ነው፣ መንፈስ እንደ ሕይወት መፍሰስ ወንዙ ነው፣ ይህም የሚፈስሰው ሦስታንዱ አምላክ "ወደ ዘላለም ሕይወት ውስጥ" ነው፣ ይህም እንደ የዘላለም ሕይወት ጥቅል-ድምር (በእግዚአብሔር እንደ የሕይወት ክብር፣ በአብ እንደ የሕይወት ብርሃን፣ በወልድ እንደ የሕይወት ዛፍ፣ እና በመንፈስ እንደ የሕይወት ወንዝ ያሉበት) አዲሲቷ ኢየሩሳሌም መሆናችን ነው—4፡14፤ ራእ. 21፡9-11፣ 23፤ 22፡1-2፣ 5።

ለ. ክርስቶስ እንደ ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ቃል በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ውስጥ ተገልጧል—ቁ. 1፦

1. ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር ቃል በፍጥረቱ በኩል ለእግዚአብሔር ይናገራል—ቁ. 3።

2. ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር ቃል በተሠግዎው በኩል እንደ እግዚአብሔር ማደሪያ ድንኳን ለእግዚአብሔር ይናገራል—ቁ. 14።
3. ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር ቃል ለቤዛነት የእግዚአብሔር በግ በመሆኑ ለእግዚአብሔር ይናገራል—ቁ. 29።
4. ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር ቃል ለአዲሱ ኪዳን የእግዚአብሔር ቤት (ቤቴል) ሕይወታዊ በሆነ መልኩ ለመገንባቱ በእግዚአብሔር የተዋጁት ሕዝብ ወደ ድንጋይነት ለመለወጣቸው የሚቀባው መንፈስ በመሆኑ በኩል ለእግዚአብሔር ይናገራል—ቁ. 32-42፣ 51፤ ተዛ. ዘፍ. 28፡11-22።

ሐ. ቃል ሥጋ የሆነው እግዚአብሔር የሚነካ፣ የሚቀበሉት፣ የሚለማመዱት፣ የሚገባበት፣ እና የሚደሰቱት ለማድረግ ነው፣ ይህም ራሱን ወደ እኛ ውስጥ መሥራት ይችል ዘንድ ነው—ዮሐ. 1፡14፤ 14፡16-17።

መ. እንደ እስትንፋስ እንድንተነፍሰው፣ እንደ ሕያው ውሀ እንድንጠጣው እና እንደ ሕያው እንጀራ እንድንበላው ክርስቶስ መንፈስ ሆኗል—4፡10፣ 14፤ 6፡32-33፣ 35፣ 51፣ 54-57፤ 7፡37-39፤ 20፡22።

ሠ. ክርስቶስ እውነተኛው የወይን ተክል ነው፣ እኛም ቅርንጫፎቹ ነን—15፡1-8፡-

1. የወይኑ ተክል ሕይወት፣ ውስጠ-ነገር እና ባህሪ የቅርንጫፎቹ ሕይወት፣ ውስጠ-ነገር እና ባህሪ ነው—1 ዮሐ. 5፡11-12፤ 2 ጴጥ. 1፡4።
2. ወልድ እንደ የወይኑ ተክል የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ማዕከልና የአብ ብልጥግናዎች ሁሉ አካል መልበስ ነው፤ አብ ወልድን በመንከባከብ፣ ከብልጥግናዎቹ ሁሉ ጋር ራሱን ወደ ወይኑ ተክል ውስጥ ይሠራል፣ በመጨረሻም፣ የወይኑ ተክል እንደ ቅርንጫፎቹ በክርስቶስ ውስጥ በሆኑ አማኞች በኩል ብዙዎች በተካተቱበት መንገድ አብን ይገልጣል።

ረ. ውስጠ-ልምምዳዊ በሆነ መልኩ ክርስቶስን መለማመድ በእውነቱ ሕይወታችንና የማንነታችን ይዘት ለመሆን ክርስቶስ ራሱ ወደ እኛ ውስጥ መግባቱ ነው—ቆላ. 3፡4፣ 10-11።

## III. የዮሐንስ ወንጌል ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቱ ውስጠ-ልምምዳዊ እውነቶችን ይገልጣል፡-

ሀ. ጌታን ወደ ውስጣችን የመቀበላችን ውጤት የቤተ ክርስቲያን ክፍሎች እንድንሆን ነው—12፡24፤ 20፡17፤ 15፡4-5፤ 3፡29-30።

ለ. የጌታ ምለሳ ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት ተግባራዊ ልምምድ ውስጠ-ልምምዳዊ በሆነ መልኩ ክርስቶስን መለማመድን ለመመለስ ነው—ገላ. 1፡15-16፤ 2፡20፤ 4፡19፤ 1፡2፡-

1. ውስጠ-ልምምዳዊ የክርስቶስ ልምምዳችን ውጤት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ወደ አማኞቹ ውስጥ የተቀናበረው ክርስቶስ ናት—ኤፌ. 3፡16-19።
2. የሞተውና ከሞት የተነሣው ክርስቶስ አካሉ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን ለማፍራት ወደ እኛ ውስጥ ተሠርቷል—ቆላ. 1፡27፣ 18፤ 2፡19፤ 3፡15።
3. ክርስቶስ በራሱ የአካሉ ራስ ነው፣ ወደ እኛ ውስጥ የተቀናበረው ክርስቶስ ደግሞ አካሉ ነው—ኤፌ. 1፡22-23፤ 3፡17፤ 4፡15-16፤ ቆላ. 1፡18፣ 27፤ 3፡4፤ 2፡19፤ 3፡15።

ሐ. ምንም እንኳን *ቤተ ክርስቲያን* የሚለው ቃል ልዩ በሆነ መንገድ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ጥቅም ላይ ባይውልም፣ የቤተ ክርስቲያን ሕልውና እና ቤተ ክርስቲያንን የሚያዋቅሯት ክፍሎች ሃቅ በግልጽ ተብራርቶአል፣ ቤተ ክርስቲያንም በሰባት መንገዶች ተመላክታለች፡-

1. ቤተ ክርስቲያን ከብዙ የስንዴ ቅንጣቶች የተዋቀረች ናት፣ እነዚህም በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኩል የፈሩ ብዙ አማኞች ናቸው—12፡23-24።
2. ቤተ ክርስቲያን ከጌታ ብዙ ወንድሞች የተዋቀረች ናት—20፡17።
3. ቤተ ክርስቲያን የአብ ቤት ናት—14፡2፣ 23።
4. ቤተ ክርስቲያን ብዙ ቅርንጫፎች ያሉት የወልድ የወይን ተክል ናት—15፡5፣ 7።
5. ቤተ ክርስቲያን በተጠናቀቀው መንፈስ የተወለደች፣ የመንፈስ አዲስ ልጅ፣ አዲሱ ሰው ናት—16፡20-22።
6. ቤተ ክርስቲያን ሙሽራው ክርስቶስ ያላት ሙሽራይቱ ናት—3፡29-30።
7. ቤተ ክርስቲያን እረኛው ክርስቶስ ያላት አንዲ መንጋ ናት—10፡14-16።

መ. ተግባራዊው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጠ-ልምምዳዊዎቹን እውነቶች የመለማመዳችን ውጤት ነው፤ ውስጠ-ልምምዳዊዎቹን እውነቶች ስንለማመድ፣ ቤተ ክርስቲያን ቅጽበታዊ በሆነ መልኩ ትፈራለች—ሮሜ. 8፡10-11፤ 12፡4-5፤ 16፡1፣ 4-5፤ 1 ቆሮ. 1፡9፣ 30፤ 15፡45፤ 6፡17፤ 1፡2፤ 12፡27።

1. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እኛ ሁላችን ሦስት ማዕዘናዊ ገጽታ ያለን የቤተ ክርስቲያን ክፍሎች መሆን አለብን—“ማርታ-አልአዛር-ማርያም።”
2. በእውነተኛው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ትጉህ የሆነው አገልግሎት ለጌታ ይቀርባል፣ የጌታ ሕያው ምስክር ይታያል፣ ለጌታ ያለው ፍጹም ፍቅር ይፈስሳል፤ ይህ ጌታን የምትይዝና የምትገልጥ መያዣ ዕቃ የሆነችው የጌታ አካል እውነተኛው መገለጥ ነው።

*© 2021 Living Stream Ministry*